# “የሚጥምህን አንተ ታውቃለህ!”

*በላይነህ አባተ* *(abatebelai@yahoo.com)*

በልጅነት ዘመኔ አንድ የእግዚአብሔር እንግዳ ሲጓዙ ውለው ለአይን ሲነሳ “የመሸበት ሽማግሌ፤ አሳድሩኝ!” ብለው በደከመ ድምፅ ጠየቁ። ያው እንደምታውቁትና የናንተም ቤተሰብ እንደሚያደርገው የኔም ቤተሰብ የተሸከሙትን ጓዝ አውርዶ “ቤት-ለእግዚአብሔር እንግዳ!” ብሎ በደስታ ተቀብሎ አስተናገዳቸው። ወዲያውኑ እጃቸውን ታጥበው፣ ምግብ ቀርቦልቻቸው፣ መጠጧን ቀመስ አድርገው  ድካማቸውም ለቀቅ ሲያደርጋቸውና አንደበታቸው ፈታ ሲል ጨዋታ ጀመሩ። የጨዋታ ለዛቸው ዛሬ እንኳን ከአይኔ ላይ ነው። ዳግም የማግኘት እድል ቢኖረኝ ኖሮ እንኳን ለአንድ ቀን ለወርም የእግዜር እንግዳ ባደርጋቸው ደስ ባለኝ ነበር። እንደሚታወቀው በጠቢያ ባህል አዋቂ ሲጫወት ልጅ ወይ ወደ ውጪ መውጣት አለበት አለዚያም ከዚያ ዘወር ብሎ መቀመጥ ይኖርበታል። ይህንን ያላደረገ ልጅ  እንደ ቆላ በርበሬ ሲቆጠቁጥ የሚውል የመንኩሴ ቁንጥጫ ይከተለዋል። የመነኩሴ ቁንጥጫ እንዴት እንደሚጠዘጥዝ የቀመሰው የኔ ቢጤ ሁሉ ያውቀዋል። ተመልሸ ልጅ መሆን የማልፈልገው ይህንን ካሰብኩ ብቻ ነው። ታዲያ ይህ የቤት ደንብ ስላለ እኔም የእግዚአብሔር እንግዳው ሽማግሌ ሲያወሩ  ወይ ወደ ውጪ መውጣት አለዚያም ዘወር ብዬ  መቆየት ነበረብኝ።

ጨዋታቸው እንኳን ለአዋቂዎች ለእኛ ለልጆችም እነደከረሚላ የሚጥም ስለነበር በዚያን ሰዓት ሁለቱን ክፍሎች ከሚያገናኘው ስፍራ ላይ ላመል ያህል አካሌን እንዳያዩት በግርግዳው ከልዬ ጆሮዎቼን ግን እዚያው ቤተሰብ፣ በእንግድነት የነበሩት ዘመዶችና ጎረቢቶች ተሰብስበው ከሽማግሌው ጋር ከሚያወኩበት ቦታ ላይ ጣል አደረጌ ማዳመጥ ጀመርኩ። ይህችን ደብቄ የኖርኳትን ምስጢሬን ስላወጣሁ እኔን “ይህ ሰው ወሬኛ መሳይ ነው፣ ለወሬ ሞትኩ ባይ ሳይሆን አይቀርም፣ በልጅነቱ ይሸንን ያህል ወሬ ይናፍቅ ከነበረ ዛሬማ ምንም ቁም ነገር ሳይሰራ ወሬ እነደ ውኋ ሲቀዳ የሚውል ከንቱ ሳይሆን አይቀርም ወዘተርፈ ” እያላችሁ በማውጣት በማውረድ ወይም በመጠቋቆም የምታወጉ ካላችሁ ወግና ጨዋታውን ያሳምርላችሁ ከማለት በስተቀር ሌላ እምለው የለኝም። ሐሳብን ለመግለጥ የሚያፍን መቼ አጥታችሁ ታውቃላችሁና እኔ ደግሞ ልጨመርባችሁ! ዳሩ ግን በኔ ወሬ ወዳጅነት እየተገረማችሁ የእግዚአብሔር እንድግዳው ሊያስተላልፉት የፈለጉትን መልእክት እንዳትዘነጉ በአክብሮት እጠይቃለሁ።  ወዲያውም የአገር ልጅ ሲያወጋ በይሉኝታም ቢሆን “እህ!” እያሉ ጨዋታን ያስጨርሷል።

እንግዳው “አንድ ቀን” አሉ  “አንድ ቀን፤ ቅዳሜ ቀን!” አሉ አሁንም ቀጠሉና? “የሆሳእና ለት ቅዳሜ ቀን አንድ ሰው ገበያ ይኸዳል። ለፋሲካ በግ ሊገዛ” አሉ። “ምነው ሰውየው ቅዳሜን እንደ ዳዊት ደጋገሙ ቅዳሜ ቀን ነው እንዴ የተወለዱት አለች” አንዷ እኔ ባለሁበት በኩል ተቀምጣ የነበረች አድማጭ በአሽሙር ቀስ ብላ (የሰሟት አይመስለኝም)። ብዙው አድማጭ ግን “ እህ…” እያለ ሙሉ ልቡናውን ሰጥቶ ያዳምጣቸው ነበር። ይቀጥላሉ ብሎ ሰው በአንክሮ ሲጠባበቅ እርሳቸው ግን ብርጭቆዋን በሰፊ እጃቸው ሳብ አድርገው ወስደው ከከንፈራቸው አስማሟት። የተጎነጩትን መጠጥ አፋቸው ውስጥ እንደሚታኘክ ምግብ አዘዋውረው አጣጥመው ወደ ታች ከላኩ በኋላ “እየሰማችሁኝ ነው?” ብለው ጠየቁ። አሁን ሳስበው ይህንን ጥያቄ የጠየቁት ጨዋታው በተንጠልጠል የቆየበት ምክንያት በእርሳቸውና በብርጭቋቸው መሳሳም ምክንያት ሳይሆን በአድማጮች አለመከታተል መክንያት መሆኑን ለማስመሰል የፈጠሩት መላ ይመስለኛል። ሆኖ ካልተገኘም የውድማው አማኑኤል ይቅር ይበለኝ።  አንድ ሁለቴ ሳብ ካደረጉ በኋላ “ይህ በግ የሚገዛው ሰውየ ከተሜ ነኝ ባይ ነው፤ እንደነዚህ እንደምታይዋቸው አስኳላ ተማሮች በኮት ነው እሚሄደው!” ብለው እኛን ተማሮችን ለመፈለግ ቢያጣብሩ ባይናቸው ብረት አልገባ አልን። “ዛዲያ በግ-ተራ ኸደና አንዱን እንደዚህ ጉቦ እስታፍንጫው በልቶ እንደደለበ አገር-ገኘ ሰብቶ የሚያለከልከውን በግ መርጦ መጀመሪያ ላቱን በሁለት እጁ አንስቶ ነቅነቅ ነቅነቅ እያደረገ መዘነ። ከዚያም ዘወር ብሎ ከፊቱ በኩል ሄዶ በበጉ የፊት እግሮቹ መካካል ቀኝ እጁን አስገብቶ እንደምታምጥ ሴት “እ..እ..” እያለ እያቃሰተ ብድግ አደረገና አሁንም እንደ አቁማዳ ጤፍ መዘነው። ከዚያም በጎን በኩል ሆኖ ወገቡን ጥስቅ አርጎ ይዞ ጨምቆ ይዞ አሁንም በጉ የያዘውን የስጋ መጠን በልቡ አሰላሰለ። ከዚያም በርቀት ቆሞ አይኑን አንዴ ከፊት ሌላ ጊዜ ሸውረር እያደረገ፤ ከወገቡ ዝቅ ከፍ እያለ አሁንም በጉን አገላብጦ ቀለሙ እስቲለቅ  ተመለከተው።  ከዚያ …” አሉና አሁንም የጀመሩትን ሳይጨርሱ  እስከወገቧ ድረስ ጎደል ያለችዋን ብርጭኳቸውን አነሱና ሲምጉት እንዳልቆዩ ሁሉ መጠጡን አንዴ በውጪ በኩል ሌላ ጊዜ በብርጭቆው አፍ በኩል አገላብጠው ተመለከቱት። አስተናጋጁ የዚህ አይነቱ መላ ስለገባው ይመስለኛል ፈጠን ብሎ ሄዶ ብርጭቋዋን ተቀብሎ በጥንቃቄ ሞላና እንኾ ብሎ ሰጣቸው። “ኑሮህን እንዲህ ይሙላልህ ልጄ!” ብለው መረቁና ጢም ያለው እንዳይፈስ አንድ ሁለቴ ፉት ብለው ብርጭቆዋን በጥንቃቄ  ከእግሮቻቸው መካከል አስቀምጠው ወደ ጀመሩት ነገር ተመለሱ።

“ ሻጭ ደግሞ” አሉ “ሻጭ ደግሞ ራሱን በሶስት ዙር ፎጣ ጠቅሎ፣ ጅንፋም (እንግዳ ለሆነባችሁ ጅንፍ ሰዎች ሲጣሉ ሰው ለመፈንከት እንዲመቻቸው በዱላ ጫፍ ላይ የሚያስገቡት ክብ ብረት ነው) ዱላውን በግራ ብብቱ በኩል ተመርኩዞ፤ በቀኝ እጁ ጥርሱን በወይራ እንጨት እየፋቀ ፈንጠር ብሎ ተጀንኖ ቆሞ ገዥው የሚያደርገውን ሁሉ በአይነ ቁራኛ ይመለከታል። ገዥ ደሞ ያን በግ አገላብጦ ታየ በኋላ ወደ ሻጩ እንደመጠጋት ብሎ “ባለ በግ! አለ ጮክ ብሎ”። ሻጭ በፈንታው ኩታውን አፍንጫው ላይ ጣል አርጎ፤ ተንጠባሮ ደረቱን ነፍቶ በኩራት ቆሞ ባፍንጫው እየተናገረ  “ወዲህ..!” አለ። እንዲያው ሆነ ብሎ ላስተዋላቸው የሚጣሉ እንጅ የሚገበያዩ አይመስሉም ነበር” አሉ የሚያዳምጧቸውን ሰዎች በአንክሮ እየተመለከቱ። “ገዥም በበኩሉ ቆጣ ብሎ ስንት ትሸጣለህ?”  ብሎ ጠየቀ።  ሻጭም የተከናነበውን ነጠላ ከአፍንጫው ላይ በቀኝ እጁ ላፍታ ወረድ አድርጎ  “አርባ ብር” አለ በጎረነነ ድምጥ። (ዛሬ በግ ሁለት ሺህ መግባቱን አትዩ አርባ ብር ያኔ ብዙ ነበር)። በዋጋው

መናር የደነገጠ ገኘሮም ትቶ ለመሄድ ፊቱን መለስ አድርጎ **“በአርባ ብርማ አህያ አልገዛም!”** ብሎ ሳይጨርስ አህያ በምሳሌትነት በመቅረቡ ስጋውም ደሙም እንደመሞቅ ያለ ሻጭም ***“የሚጥምህንማ አንተ ታውቃለህ!!”*** ብሎ መለሰለት ብለውን አረፉ። ሳል ያለበት ሰው ስርቆት መሄድ የለበትም ይባላል። አዋቂ ሲያወራ መኖር ያልነበረብኝ እኔም የቤት ደንብ አለማክበሬን ሌሎች ሲስቁ አብሬ ተክተክ ብዬ የሳኩት ሳቅ መሰከረብኝ። ሳስበው ዛሬም ቢሆን ቻይና ወይም ኩባ ላላደገ ሰው “የሚጥምህን አንተ ታውቃለህ” ጉዳይ ባያስቅ ወይም ፈገግ ባያደርግ እንኳ የሚገርም ይመስለኛል።

መልካም መልካሙ አልወራ ወይም ደግሞ እንደ ሞኝ እያስቆጠረ ነው እንጅ ወለደ-አፍሪካዎችን በተለይም ጦቢያውያንን ከአብዛኛው የአለም ሕዝብ ልዩ የሚደርጋቸው ነገሮች ብዙ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ከላይ እንደተጠቀሰው እንግዳ በእንግዳነቱ ለባለቤቱ የሚሰጠው ክብር፣ እንግዳ ተቀባዮችም ለእንግዳ አብሶም ለእግዚአብሔር እንግዳ ያላቸው ክብር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከራሱ ጎሳ ጋር ካልሆነ በስተቀር ከሌላው ጎን አብሮ መኖር አይችልም እያሉ አሁን አሁን የዘር ጉንጉን የሚሸርቡለት ቀረ-በከንቱዎች እንደሚሉት ሳይሆን ምርጥ ምርጡን ለእንግዳ የሚያበላ፣ ውብ ውቡን የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ ለመጣ ሁሉ የሚያጠጣ፣ አልጋውን ወይም የሚተኛበትን መደብ ለእንግዳ የሚለቅ፣ ፀጉረ-ልውጥ በመጣ ቁጥር ተጨንቆ ተጠቦ የሚያስተናግድ፣ መልካም ስራውን ምላሱ ሳይሆን ምግባሩ የሚገልጸው ሕዝብ ነው። ታዲያ ይህንን በብሉይ ኪዳን(1) ድልድይነት ከመለኮት ጋር የተያያዘ ባህሪውን እንደ ድክመት በመቁጠር የውጭ ሰዎች የእግዚአብሔር እንግዳ መስለው ቤት ለንቦሳ እያሉ እየገቡ ሙዳዩን ሳይቀር እየከፈቱ ያጠኑታል፤ ይሰልሉታል።

አገር ውስጥ የበቀሉት ከንቱዎች እንደዚሁ አንዴ ከእግዚአብሔር የተላክን ነን ሌላ ጊዜ ነጻነት ቅርቀብ ጭነን የመጣን የምንትስ ነጻ አውጭ ነን እያሉ ካለ እርካብ እንጣጥ ብለው ዘለው እየወጡ እንደ በቅሎ ለጉመው በሜዳውም በተራራውም ይጋልቡታል። ገንዘብ ይዘው ለሚመጡ የውጭ መንግስታት ሁሉ በፈቃደኝነት ሎሌ ሆነው እየተቀጠሩ እነዚህ አገር በቀል ከንቱዎች የራሳቸውን ሕዝብ ለውርደት ይዳርጉታል። ለፋሽሽት ጣልያን የልብ ውጋት ሆኖበት የነበረው በላይ ዘለቀ ማርያም የእየሱስ ወላጅ በመሆንዋ በጣም ያከብራትና ያመልካትም ነበር እየተባለ በሰፊው ተነግሯል። (2) ይህንን ባህሪውን የሞሶሎኒ ጀኔራሎች እንደ ድክመት በመቁጠር መቀመጫ መቆሚያ ባሳጣቸው ቁጥር “በማርያም ይዘንሃል ተወን!” እያሉ ይለምኑት ነበር ይባላል። ተንኮላቸው የገባው ይህ ጎብዝ ግን “የአንተ አገር ማርያም ካልሆነች የኤይቱ አገር ማርያም እንደ አሞራ ከንፋችሁ የሰው አገር ውረሩ አትልም የሚል መልስ እየሰጠ አገር የማዳን ስራውን አሳምሮ አጠናቋል። እንደ አለመታደል ሆኖ ግን እኛ እስካሁን በመተንፈስ ላይ ያለነውን ከውጭ ሀይሎች ባርነት ነጻ የመሆን እድል ለአራትና ለአምስት አመታት እንኳን ሳይተነፍስ፤ ለፋሽሽት ያልተንበረከከው አርበኛ፣ ለዘላለም ደረታችንን ነፍተን፣ ትከሻችንን ቆልለን፣ እጃችንን በኪሳችን ከተን ስንንቀባረር እንድንኖር የሚያደርግ የማይጠወልግ የነጻነት መንፍስ ያርከፈከፈብን ጀግና፤ ወራሪ የተበተበው የስለላ መረብ ያልጠለፈው ወንድ፣ በመጨረሻ በባእዳን ሳይሆን አምኖ ክንዱን በሰጣቸው የአገሩ ልጆች እጅ ታንቆ በልጅነት እድሜው ተቀጭቷል። (3) በእውነት ደግነት እንዲህ እያደረገ ሲያስጠቃ እጅጉን አያሳዝንም? እውንን እግዚአብሔር በዚህ አለም ውስጥ አለ ወይ ብሎስ አያስጠይቅም?

ቤተ-መንግስት መሆን ሲገባው “ቤተ-ሰይጣን” ሆኖ ያረፈው አራት ኪሎ የሚገኘው የተንኮልና የሸር መጎንጎኛ ግቢ በእውነቱ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከምዕራብ የሚገኘው የእያንዳንዱ ዜጋ ንብረት ነው። አዎ የእነ ጦና፣ ሽምሰዲን፣ ደሌቦ፣ ሮባ፣ ሁሴን፣ አድማሱ፣ አብረኸት፣ እነዘበርጋ፣ ኦባንግና ሌሎችም የራሴ ሊሉት የሚገባ ግቢ ነው። የተሰራው ወይም የተገነባው ነገሥታት ነን ይሉ የነበሩት ወይም ከዚያ በኋላ የመጡት ከንቱ ፍጡራን እንጨት ቆርጠው፣ ድንጋይ ተሸክመው፣ ጭቃ ወይም ስንሚንቶ አቡክተው አይደለም። የተገነባው ዛሬ በ21ኛው ክፍለ-ዘመን እንኳን በአዱማ እየቆፈረ ማሽላ በሚዘራ ገበሬ ነው። የተሰራው በየቁራንቁሩ የሚኖር ድሃ እሚጠ ግብር እየገበረ፣ ተገዶ እየወጣ ጭቃ እስከ ጉልበቱ እየዋጠው እያቦካ፣ ዛፍ እቆረጠ፣ የተቆረጠው ዛፍም ወገቡ ላይ እየወደቀ ሳይጠገን ወይም ሳይታከም-የቀረ ሰባራ እያደረገው ነው። የሚጠገነውም አገሪቱ ውስጥ ከአልፋ እስከ ኦሜጋ ያለው ሕዝብ የሚበላው ሳይኖረው እየገበረ ነው።

ድሃ ሕንጻውን ሰርቶም በቃህ አይባልም። እርሱ አንድ ቁምጣ አስራ አምስት አመት እየለበሰ በዙፋን ላይ ቤተ-መንግስት ያስቀመጣቸውን ሱፍ ያለብሳል፤ በወርቅና በአልማዝ ያሽቆጠቁጣል። እርሱ ለእንቁጣጣሽ እንኳን አሬራ ሳይቀምስ እነሱን ጮማና ብርንዶ በነጋ በጠባ ያስቆርጣል። እርሱ አንድ ቀን ሁለት ቀን ተጉዞ በአህያ እየጫነ ድፍርስ ውሃ እየጠጣ እነርሱን በውስኪ ያራጫል። እርሱ በሌላው አለም ታሪክ ሆነው በቀሩት በተስቦ፤ በወባና በሳንባ ነቀርሳ እያለቀ እነሱን ውጭ እየላከ ያሳክማል። እርሱ አውራ ጣቱን ወደኋላ ቀስሮ እየፈረመ እነሱንና ልጆቻቸውን አውሮጳና አሜሪካ እየላከ ያስተምራል። በዚህም አያበቃም። መከራውና ብሶት በዝቶበትና መሮት ማንጎራጎር ሲጀምር ተቀፍድዶ ይታሰራል፤ ከስራ ይባረራል፤ ያለችውን ንብረትም ይቀማል። መከራው በዚህም አይቋጭም። የስልጣን ተቀናቃኝ፣አድሃሪ፣ አደገኛ ቦዘኔ የሚሉ ስሞች እየተሰጡት በኮረንቲ ይተኮሳል፣ ይሰቀላል ወይም በባሩድ ህይወቱን ያጣል። ገዥዎች ሕዝብን እንደ ጎመን ጥልቅ ከሆነ ድስት ውስጥ ከተው ከታች እሳቱን እየቆሰቆሱ ከላይ ተንፍሶ ወይም ገንፍሎ እያንዳይወጣለት ደግሞ ከባድ መግላሊት(ክዳን) ከድነው ሙክክ አድርገው እየቀቀሉ ከጥቅም ውጪ ያደርጉታል። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ይህንን የሚያደርጉት ሲመጡ አንድም ከእግዚአብሔር መንበር የተላክን ቅዱሳን አለዚያም ነጻነትን እንደ ወተት ልንግትህ የመጣን ምጥአቶች ነን እያሉ የአገር ሕዝብ በጋራ ከሰራው ቤት ውስጥ የራሳቸውን ቤተ-ሰቦች ወይም ጓደኞች ሳይቀር በሸርና በተንኮል እያጠፉ በእንግድነት ሶስት-አራት አመት ቆይተው ለመውጣት ሳይሆን እስተንፋሳቸው ሲው እስከምትል እዚያው ለመኖር ቆርጠው ዘው ብለው የሚገቡ ከንቱ መልእክተኞች ናቸው።

በጦቢያ ምድር ብቻ ሳይሆን በአብዛኛው የአፍሪካ አገሮች “መሪዎች ነን” (4) የሚሉት ሁሉ ሕዝብ በነቂስ ወጥቶ የመረጣቸው ወይም የእግዚአብሔር እንግዳ አሳድሩን ብለው ሕዝብ ከሰራው ቤተ-መንግስት ግቢ በጊዜአዊነት የገቡ ሳይሆኑ የሰውን ልጅ በወታደር ጫማ እየረገጡ ወይም በውጭ መንግስታት ፈቃድና ርዳታ እዚያው ኖረው እዚያው ለመሞት

በመቁረጥ ተንደርድረው የገቡ ናቸው። እነዚህ በየአመቱ "የአፍሪካ አገሮች መሪዎች ስብሰባ" እያሉ አዲስ አበባ በሚገኘው የአፍሪካውያን አዳራሽ የሚሰበሰቡት ገኸሮዎች የአንድ እናት ልጆችን ያህል ተመሳሳይነት አላቸው። አዎ ከሶስት ወይም ካራቱ በስተቀር ብዙዎቹ  አእምሯቸውን ሳይሆን ጡንቻቸውን ተማምነው የሚኖሩ ናቸው። ሕዝብ ወዷቸው ሳይሆን ፈርቷቸው እየተንቀጠቀጠ እንዲኖር የሚሹ የኢዲያሚን ደቀ-መዝሙራን ናቸው። በእዉነቱ እነዚህ ፍጡራን ለእግዜር ቀርቶ ለሰው ልጅ እንኳን ቁልጭ ብለው በሚታዩ ስንክሳር ሐጥያቶች የተዘፈዘፉ ናቸው ብሎ የማያምን አለን? እንደጌ እንደጌ ደርጃው ወይም መጠኑ ይለያይ እንጅ ሕዝብን አረጋገጣቸው፣ የሕዝብን ገንዘብ አዘራረፋቸው፣ ለውጭ መንግስታት አገልግሎት አሰጣጣቸው ወዘተ ሁሉ ካርቦን ቅጅ ነው የሚመስለው። ሌላው ቀርቶ የሕዝብን ድምጽ አሰራረቅ ጨቅላዊ ባህሪያቸው ሁሉ አንድ አይነት ነው። ካለተፎካካሪ መወዳደር ወይም የምርጫ ካርድ ኮረጆ ቀምቶ መሮጥ በአፍሪካ ምድር እንደ ባህል እየሆነ መጥቷል! ታዲያ ሳይወዳደሩ ከሚያሸንፉ፣ እንደ ልጅ "ጨዋታ ፈረሰ! አባይ ደፈረሰ!" ብለው ጠብ ከሚፈጥሩ ጉዶች ምን ይጠበቃል? በእነሱ ምክንያት ስንቱ ሕጻናት፤ አሩግና እንደዚሁም ወጣት በርሃብና በበሽታ በማለቅ ላይ ይገኛሉ? በእነዚህ ፍጡራን ምክንያት ስንት ፍትህ ፈላጊዎችን ተገለዋል፣ ታስረዋል፣ ተሰደዋል ወይም ደግሞ የደረሱበት እንዳይታወቅ ተደርገዋል? በእነሱ ምክንያት ስንቱ እንዳይሰማ፣ እዳያነብ፣ እንዳይናገር እንዳይጽፍ አንደበቱ ተዘግቶ ይኖራል?  በእነሱ ምክንያት የስንቱ አፍሪካዊ አእምሮ ድርቅ እንደገባው ሰብል በመቀጨጭ ላይ ይገኛል? በእነዚህ ሰዎች ምክንያት የስንት አፍሪካውያን ተስፋ እንደ ክረምት ሰማይ ጨልሞ ይገኛል? የዘላለም መሳቂያ፣ መሳለቂያና መዘባበቻ በመሆኑ ስንቱ በመላው አለም የሚኖር የጥቁር ዘር አዝኖና ተክዞ አንገቱን ድፍቶ ይኖራል?

ለፈለገው ስልጣንም ሆነ ገንዘብ ነፍሰ-ገዳይ ወይም አረመኔ ሳይሆኑ እኮ መገኘት የሚችል ነገር ነው። መልካም ከሆኑ እኮ ለብዙ ጊዜ በሕዝብ ፈቃድ ስልጣን ላይ መቆየት ወይም ደጋግሞ ባለስልጣን መሆንም ይቻላል።  ደህና ነገር ይዘው ቢመጡ፣ ለትውልድ በጎ ራእይ ቢኖራቸው እኮ ከዙፋን ልውረድ ቢሉ እንኳን ሕዝብ  በእግዚያብሔር እዚያው ቆዩልን ብሎ ይለምናል! ሕዝብን እንደ ግዑዝ መቁጠር ቢያቆሙና ለሰው ልጅ ህይወት ክብር ቢኖራቸው እኮ በስላሶች ወይም በአላህ ከዚያው ቆዩልን ብሎ ልጅ አዋቂው ከእግር ላይ ይወድቃል!  እግዜር የሰጠውን ልሳኑን ባይዘጉት፣ ሰላይ በየደጁ ባያስቀምጡበት፣ ባያንገላቱት፣ ባያስሩት፣ ባይገሉት እኮ ሕዝብ የዚህን መንግስት እድሜ አርዝምልን ብሎ ሌት ከቀን ደጀ-ሰላም ወይም መስጊድ ፊት ተንበርክኮ ይጸልያል! በራሳቸው ሕዝብ ወገብ ላይ ቆመው የሌሎችን ትከሻ ሲስሙ ባይውሉ፣ የአገራቸውን ጥቅም ራሳቸው ማመልከቻ እያስገቡ ባይሸጡ፣ የቤታቸውን ትተው የሰው ቤት ማገር ሲያጠነክሩ ባይውሉ እኮ ክርስቲያኑ ሃሌ-ሉያ ብሎ  የቤተ-ክርስቲያኑን ደወል ይደውላል፤ እስላሙም ወ አላህ ክበር ብሎ ዶሮ ሳይጮህ ምስጋናውን ለሃያሉ አላህ ያደርሳል።

ለመሆኑ እኛ ሰው ሆነን የተፈጠርን ፍጡራን ወደ አርመኔነትና ወደ ህሊና ቢስነት የምንቀየረው ብዙ ዘመን የምንኖር እየመሰለን ወይም ሞት መኖሩን እየዘነጋን ይሆን?  እድሜአችን ዘለግ ብሎ መቶ አመት የመኖር እድል ቢገጥመን እንኳን ይህ በምድር ላይ የምንኖርበት መቶ ከማንኖርበት የትየ ለሌ(infinity) ዘመን ጋር ሲወዳደር በአይን ከማይታዩት ቫይረሶችም ርዝመትም እጅግ በጣም ያነሰ ነው። በእርሱ አምሳል የተፈጠርን ሰዎች ይህንን ሁሉ ግፍ የምንፈጽመው ምናልባት ጽድቅና ኩነኔ  የለም እያልን ይሆንስ ይሆን? ጽድቅና ኩነኔ መኖርኑን ተጨባጭ በሆነ መንገድ ባናረጋግጥም እኮ አለመኖሩንም በትክክል የምናውቅ አይመስለኝም። በበኩሌ "ጽድቅና ኩነኔ እንደሌለ ቀብር ውስጥ ገብቼ ወይም ቤተ-ሙከራ ውስጥ ፈትሼ አረጋግጫለሁ" ያለ ሰው ወይም ሳይንቲስት መኖሩን እስካሁን አላውቅም። በነግፍ-አይፈሬ መንፈስ እንመራና እሽ ጽድቅና ኩነኔ የለም እንበል። የጠቢያ አቀንቃኝ እንዳለው ጽድቅና ኩነኔ ባይኖርስ ከክፋት ደግነት አይሻልም ወይ? ሕዝብን በሰቆቃ ድስት ውስጥ ሳይቀቅሉ ሆድን በጎመንና በድንች ሞልቶ ማደር አይቻልም ወይ? በሰው ላይ በሐሰት ሳይመስክሩ፣ ነፍሰ-ገዳይን ሳያገለግሉ፣ የአገርን ሕዝብ ከሚያስለቅሱት ፍጡራን ጋር ሳይሰለፉ ባቄላ ንፍሮ ጥሽቅም አርጎ በልቶ ማደር አይቻልም ወይ? አንድ ስንዝር እድሜ ለመኖር ስንል ለማንኖርበት የትየ ለሌ ዘመን ሂትለር፣ ስታሊንና ኢዲአሚን በቋሚ አባልነት ከተመዘገቡበት ቡድን ጋር መቀላቀልን ምን አመጣው? እንዲህ አይነት ጭንቅ ያለ ነገር ሲገጥማቸው "ሳይቸግር ጨው ብድር!" ይሉ ነበር እማማ ታንች-ወዲያ። ነፍሳቸውን ይማር።

የትኛውን ምርምር ሰርተህ ትዘከዝካለህ ብላችሁ እንደ ኮረንቲ ሽቦ አትወጥሩኝ እንጂ በኔ መላ ምት የሕዝብ ጥያቄ ውስብስብ ወይም ገደብ ያጣ አይመስለኝም። ሕዝብ ስልጣን ላይ የወጣው ዱባለ ይሁን  ኪባኪ ብዙ ግድ የሚሰጠው አይመስለኝም።  እንደምገምተው ሕዝብ የሚለው ነፍሳችሁን ከወንበር ጋር እንደ ጥጃ አትሰሩት ነው። ሕዝብ እሚለው ከሰራነው ዙፋን ላይ ተንፈላሳችሁ ህሌናችንን አታዙሩ፣ ልባችንን አታጥወልውሉት፣ ጀርባችንን አትምልጡ፣ ትከሻችንን አታጉብጡ፣ ቆሽታችችችንንም እንደ ጭራሮ አታቃጥሉት ነው። አዎ ሕዝብ የሚለው እንደገብስ እያፍተለተላችሁ፣ እንደተልባ እያሻችሁና እንደ ሽክላ እየጠበሳችሁ ሳንሞት ገሀነበ-እሳት ውስጥ አትድፈቁን ነው። በእውነት ይህ ከባድ ጥያቄ ነውን? ሕዝብ የሚለው እንደ ከፋ፣ እንደ ይርጋ ጨፌ፣ እንደ ወለጋ አለዚያም እንደ ሐረርጌ ቡና በዘነዘና ከመውቀጥም ዘላችሁ መከራና ቸነፍር ሲበዛብን ትንፋሽ ማውጣት ስንጀምር የጠይት ራትና ምሳ አታርጉን፣ አትግረፉን፣ አትሰሩን፣ ከስራ አታባሩን፣ ንብረታችንን አትቀሙን፣ ስደተኛም አታርጉን ባገራችን እንኑር ነው። አምናለሁ ሕዝብ የሚለው ለቁልቢው ገብርኤል፤ ለግሸኗ ማርያም፣ ለዲማው ጊዎርጊስ፣ ለአደባባይ እየሱስ፣ ለአክሱም ማርያም፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰማይና ምድርን በመጀመሪያዋ ቀን ፈጥሮ (1) ሰማይን ካለምሰሶ ስላቆመው አላህ ስትሉ እባካችሁ ግፍና መከራን በሕዝብ ገላና እድል ላይ መዝራት አቁሙ ነው። እውንን ይህ ውስብስብ ጥያቄ ነው ጎበዝ?

አዎ ሕዝብ የሚለው ወገኖቻችንን እየገደላችሁ ሁሌ የእድር ድንኳን ተካይ፣ ዘወትር ጥቁር ለባሽ፣ ዘወትር ፍታትና ተስካር አውጭ አታድርጉን ነው። ሕዝብ እሚለው ማምረት እየቻልን እግርና እጃችንን እያሰራችሁ፣ ማሰብ እየቻልን እምሯችንን በፍርሃት በረዶ እያገረራችሁ የርሃብና የበሽታ ቸነፍር አትልቀቁብን ነው። ነብርና ፍየል፣ ጭልፊትና ጫጩት አብረው መኖር በጀመረበት ዘመን የሰውን ድምጽ አወጣጥ ልዩነት መሰረት አርጋችሁ ክልልና አጥር እየሰራችሁ አታጉሩን፤

አታናክሱን፤ በአንድነት ሆነን እንደልባችን ተንቀሳቅሰን ሰርተን ችጋርን፣ በሽታን እናጥፋ፣ የአለም መሳቂያ ከመሆንም እንዳን ነው። ሕዝብ የሚለው ከጎሪቢት ገዥዎች ጋር ካቲካላ ስትጠጡና ጫት ስትቅሙ በስካር መንፈስ በተጣላችሁ ቁጥር የምንከባበር ሕዝቦችን በጦርነት እየማገዳችሁ አታጫርሱን ነው። የውጭ አገሮች መንግስታት ተላላኪና አገልጋይ እየሆናችሁ አታዋርዱን ነው። ሕዝብ የሚለው እንደ ሐዋርያት ደግ ሆናችሁ መልካም መልካሙን ብታድርጉ ወደ እግዚአብሔር እንጸልይላችኋለን፣ ከበሮ ይዘን እናወድሳችኋለን፣ በስማችሁ መንገድ፣ ሆስፒታል፣ ት/ቤት እንሰይምላችኋለን፣ ሐውልት እንሰራላችኋለን ነው። አዎ ሕዝብ ለዘመናት ሲል የኖረው እንደነ ጳውሎስ፣ማቲዎስ፣ ማርቆስ ወዘተ ቅዱሳን ብትሆኑ ልጆቻችንን በናንት ስም እንሰይማለን፤ በስማችሁም ታቦት ወይም ምስጊድ እናሰራለን ነው። እውንን እነዚህ ልመናዎች አጉራ-ዘለል ናቸው?

እንግዲህ የሕዝብን ጥያቄ፣ ልመና ጸሎት በመናቅ እንደበግ ደግ ሆኖ ከመኖር እንደ ቀበሮ ነጣቂ መሆን ይሻለል ብለን መደበቂያ ጉድጓድ ስንምስ የምናድረው ከሕዝብ የምንጠብቀው ንስ ምንድነው? በአምሳለ-ቅዱሳን መልክ ከምንኖር የሳጥናኤል ስርአት ተከትለን፣ እንደ ይሁዳ እውነትን እየከዳን መኖር ይሻለናል የሚያሰኝ ጤና አዳምም ሆነ ሐረገሬሳ የማያድነው ቆሌ ካለብን ሌላ ምን መድሀኒት አለው? እንደነ ማሀተመ ጋንዲ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ አቡነ ጴጥሮስ(5)ና ሌሎችም ስማችን ከሐውልት ላይ ተጽፎ ስንመረቅ ከምንኖር እንደ ሂትለርና(6) ስታሊን(7) ለጨካኞች ሁሉ ምሳሌ እየሆን ስንረገም እንኑር ብለን ቆርጠን ለተነሳኖች ምን ሐሳብ ማስለወጫ መፍትሔ አለ? የወጣንበት ሕብረተሰብ፣ ልጆቻችንንም ሆነ የልጅ ልጆቻችንን የሚኮራ በጎ ጸበል በብልቃጥ ይዘን በመምጣት ፋንታ ዘላለም ሲያሸማቅቅና ሲያሳፍር የሚኖር የጥፋት ውኃ በበርሜል ጭነን መምጣትን ለመረጥነው ከእግዚአብሔር ይማርህ የበለጠ ምን ጸሎት አለ? ተገፍትራችሁ ከምትወድቁ በማእረግ አላግባብ የያዛችሁትን ወንበር ልቀቁ፣ ቀሪ ጊዜአችሁንም በደስታ ከሕዝብ ጋር ኑሩት ስንባል አሻፈረኝ ወንበሬን ከምለቅ ወፍ አሞራው ይለቅ እያልን ከፊታችሀን ያገኘነውን እስተንፋስ ያለው ነገር ሁሉ ለመጨርገድ ቆረጥን ለተነሳኖች የእጃችሁን ይስጣችሁ ከሚል እርግማን ውጪ ከሕዝብ ምን እንጠብቃለን? ዝርዝሩ ብዙ ነው። አንገቴን ደፍቼ ባለችኝ አቅም ሳወጣ ሳወርደው የእኛን ጉዳይ የእግዚአብሔር እንግዳው ያጫወቱን በግ-ሻጭ ጨርሶታል " የሚጥምህን አንተ ታውቃለህ!" አህያ ወይስ በግ? የዘላለም እርግማን ወይስ እስከ አለም-ፍጻሜ ምርቃት? አምላክ የመጨረሻዎችን ምርጫዎች እንድንመርጥ ይርዳን። አሜን።

*ዋቢ*


1. *የሙሴ መጻሕፍት -መጽሐፍ ቅዱስ*
2. *አባ ኮስትር- በአቶ ጀምበሬ*
3. *በላይ ዘለቀ- ጌትነት እንየው (ድራማ)*
4. *The 10th African Union sumitt; http://www.africa-union.org/root/au/Conferences/2008/january/summit/10thsummit.htm (accessed on Feb 11, 2008*
5. *ጴጥሮስ በዚያች ሰዓት-ፀጋዬ ገብረ-መድህን*
6. *Hitler the rise of EVIL; http://www.imdb.com/title/tt0346293/ (accessed on 2/11/08)*
7. *Genocide Watch: Stalin Purges http://www.gendercide.org/case_stalin.html (accessed on 2/10/08)*


*የካቲት ሁለት ሺህ ዓ.ም.*